# በአግሮቢግ ፕሮግራም የድጋፍ ፈንድ ተጠቃሚዎች
# የፕሮጀክት ሃሳብ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ የወጣ 2ኛ ዙር የጥሪ ማስታወቂያ
## Agro-BIG Programme – 2nd Call for Proposals

ግብርና ተኮር የንግድ ልማትን መሰረት ያደረገ የኢኮኖሚ እድገት ፕሮግራም /Agro BIG Programme www.agrobig.org/ ከፊንላንድ መንግስት በተገኘ ድጋፍ በአማራ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ቢሮ አስተባባሪነት በትግበራ ላይ ያለ ፕሮግራም ነው።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ  አርሶ አደሮችና ሌሎች የግብርና እሴት ሰንሰለት ተዋናዮች የስራ ዕድል እንዲፈጥሩና ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ ማገዝ ነው፡፡ አግሮ ቢግ ፕሮግራም የእሴት ሰንሰልት ልማት የትግበራ ስልት (Value Chain Development Approach) የሚከተል ሆኖ በስምንት ወረዳዎች ማለትም ሰሜንና ደቡብ ሜጫ፣ ሰሜንና ደቡብ አቸፈር፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ ደራ፣ ፎገራና ሊቦ ከምከም በተመረጡ ቀበሌዎች የሚሰራ ነው። አመልካቾች የቢዝነስ ፕላናቸውን በተመረጡ እሴት ሰንሰለቶች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይመከራል። እነሱም በዋነኛነት በሽንኩርት፣ ቲማቲም ፡ድንች፣ ሩዝ፣ በቆሎ፣ ዶሮ እርባታ፣ ፍየልና በግ ማደለብና የወተት ተዋጽኦ ልማትን የሚያፋጥኑና ለዘላቂነቱ አስተዋጽኦ የሚያደረጉ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህ የመቀናጀ ድጋፍ  ፈንድ (Matching Grant Fund)  ዋናው ዓላማ ለእሴት ሰንሰለቱ ተዋናዮች የፋይናንስና የፋይናንስ አገልግሎት በማቅረብ የንግድ ሃሳባቸው ተወዳዳሪና ዘላቂ እንዲሆን ማገዝ ነው።

የዚህ የድጋፍ ፈንድ ዝቅተኛው ብር 150 ሺህ ሲሆን ከፍተኛው የድጋፍ መጠን እስከ ብር 1,000,000 ነው፡፡ አመልካቾች ቢያንስ የፕሮክቱን ጠቅላላ ወጪ 50% በጥሬ ገንዘብ መሸፈን ይጠበቅባቸዋል። ሴት አመልካቾችና የአካል ጉዳተኞች በጥሬ ገንዘብ ከሚፈለግባቸው ውስጥ ግማሹን በአይነት ማቅረብ ይችላሉ፡  ፕሮጀክቱ ተቀባይነት ካገኘ  ውል ከመፈረሙ በፊት ይህንን ገንዘብ አስቀድሞ በባንክ ማስያዝና ለዚህም ማረጋጫ የባንክ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

### 1. ማመልከት የሚችሉ አካላት

የህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች፣ የዘርፍ ማህበራት ፣ የተመዘገቡ/ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው የግል አግሮ ፕሮሰሲንግ ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶችና ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሲሆኑ አመልካቾች ቢያንስ ለአንድ ዓመት በአግሮ ቢግ የእሴት ሰንሰለት በተመረጡ ዘርፎች የሰሩ ወይንም ስራቸውን በእነዚህ የእሴት ሰንሰለት ማስፋፋት ፍላጎቱ ያላቸው፣

አመልካቾች አግሮ ቢግ ባቀፋቸው ከላይ በተዘረዘሩ 8ቱ ወረዳዎች ውስጥ ባንዱ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡ በወረዳዎች ውስጥ ያሉ ከተሞችን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም የዞን ከተሞች ባህር ዳር ደብረታቦርና ፍኖተ ሰላም የሚገኙ አመልካቾች በአቅራቢያቸው ባሉ ወረዳዎች ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር  ጽ/ቤቶች ማመልከት ይችላሉ፡፡

### 2. የፕሮፖዛል ማቅረቢያ ቅጽና አቀራረብ

ተጠቃሚ ለመሆን የምትፈልጉና መሥፈርቱን የምታሟሉ የፕሮጀክት ሃሳባችሁን ሙሉ ፕሮፖዛል (Full Proposal) ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ በማዘጋጀትና በመሸኛ ደብዳቤ የህጋዊ ወኪሉ ፊርማና ማህተም አርፎበት ከተጠቀሰው ቀን በፊት  ለየወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ የማመልከቻ ቅፁንና ተጨማሪ ማብራሪያ በተጠቀሱት በየወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ማግኘት የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን፡

### 3. የፕሮፖዛል መገምገሚያ መስፈርቶችና ገምጋሚ ኮሚቴ

የፕሮፖዛል መገምገሚያ መስፈርቶችና ቅፆች ለዚሁ ማስፈጸሚያ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ የተገለፁ ሲሆን ከእነኚህ መካከል በዋናነት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፡፡ የሚታሰበው የፕሮጀክት ሃሳብ

- የእሴት ሰንሰለት ልማት መርህን  የሚከተል ስለመሆኑ
- በተመረጡት ሰብሎች በየደረጃው እሴት የሚጨምር ስለመሆኑ
- ለአካባቢው አዲስ የአሰራር ዘይቤ የሚያስተዋውቅና ችግር ፈቺ  መሆኑ (ምሳሌ ግሪን ሃውስ ቴክኖሎጂ)

የቀጠለ................

- በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚሆኑ አካላት ብዛትና ተጠቃሚነት
- የግብይት ስርአትና የሽያጭ መጠን በሚገባ የሚያመላክት
- የስራ እድል የሚፈጥር ስለመሆኑና
- አጠቃላይ ቴክኒካዊ አዋጭነቱ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የፕሮፖዛል ምዘናና ግምገማ በየወረዳው ለዚሁ ተግባር በሚቋቋሙ የኮሚቴ አባላት አማካኝነት (የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት፣ የወረዳው ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት፣ የወረዳው ከቴክኒክና ሙያና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት፣ የወረዳው ንግድና ዘርፍ ማህበራት ተወካይ እና ከአግሮቢግ ተወካይ በተገኙበት) የሚከናወን ሲሆን ውጤቱም ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ቀርቦ በቢሮው የሚቋቋመው ክልላዊ ኮሚቴ የመጨረሻ ወሳኔ ይሰጣል፡፡ በክልል ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው ተወዳዳሪ ውል የሚፈራረመው ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ጋር ይሆናል፡፡

4. **ለየወረዳዎች የተሰጠው ኮታ**

ባለው የበጀት ውስንነት ምክንያት ሁሉንም መደገፍ ስለማይቻል ለየወረዳዎች የተሰጠው ኮታ እስከ 3 ብቻ ሲሆን ወረዳዎች አመልካቾችን በመመዝገብና በማወዳደር ከየወረዳቸው ከ1ኛ እስከ 3ኛ ብልጫ ያገኙ 3 **እጩ ተወዳዳሪዎችን ብቻ** ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በደብዳቤ ከነቃለጉባኤው መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5. **በማመልከቻው መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች**

የሚቀርበው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል የሚከተሉትን የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡
- የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና ቫት ተመዝጋቢ ከሆነ የቫት ሰርቲፊኬት ኮፒ፣
- የተሟላ ፕሮፖዛል በተገቢው ቅፅ እና በተፈቀደው የገፅ ብዛት ማቅረብ ፣ በየገጹ ማህተም የተደረገበት፣
- የሽርክና ማህበራት ከሆኑ የአባላትን ዝርዝር የያዘ መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደምብ ኮፒ፣
- ቦታ ለሚያስፈልገው የስራ መስክ የመስሪያ ቦታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ኮፒ፣
- ማመልከቻ (መሸኛ) ደብዳቤ በድርጂቱ ስራአስኪያጅ የተፈረመና ማህተም ያረፈበት፣

አመልካቾች በዚህ ማስታወቂያና በድጋፍ ፈንድ አስተዳደር መመሪያው የተመለከቱ ሁኔታዎች አሟልቶ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6. **ሌሎች ጉዳዮች**
- ከዚህ በፊት ከአግሮቢግ ፕሮግራምም ሆነ ከሌላ ፕሮጀክት ከስራው ጋር ቅርበት ባለው የስራ መስክ ድጋፍ ያገኘ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
- አንድ ተቋም ከአንድ ማመልከቻ በላይ ማቅረብ አይችልም፡፡
- በአመልካቾች አመዘጋገብ መረጣና ግምገማ ሂደት ቅሬታ ካለ የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በመሆን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡

**የማመልከቻ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን፡- ጥር 18 ቀን 2013 አም**

**የማመልከቻ ማቅረቢያ ቦታ፡- በየወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት**